# ሳስበው ሳስበው አቤና ተስፋዬ ገብረአብ አብደዋል!

ዮናስ 10/17/12

በቅርቡ ተስፋዬ ገብረአብና አቤ ቶክቻው መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎችን በነፃ እያደሉ ሳሉ መልሰው ከረሜላውን በነፃ እያደሉ የሚገኙት ኢህአዴግና አባል ድርጅቶቹ እንደሆኑ በማስመሰል በተለይም ተስፋዬ የመርዘኛው ከረሜላ ባለቤት ህወሓትንና የአማራውን ብሄረሰብ አድርጎ በየድረ ገጹና በየግሣንግሱ ጽፎ አስነብቦናል፡፡ ሆኖም ግን መርዝ የተቀቡት ከረሜላዎች ባለቤቶችና በነፃ አዳዮቹ ተስፋዬና ግብረ አበሮቹ ስለመሆናቸው ማስረጃ እያነሳን ማጣቀሻም እየጠቀስን ተጨዋውተናል፡፡

ሆኖም ግን ተስፋዬና ግብረ አበሮቹ ዛሬ ደግሞ ከድህረ ገጾችም በማለፍ በአገሬ በሚገኙና ለጥቅማቸው ባደሩ ከንቱ መጽሄቶች ሳይቀር መርዘኛውን ከረሜላ በነፃ ማደላቸውን ቀጥለውበታል፡፡ ስለሆነም እነዚህ መርዞችና መርዘኞች መርከስ ስለሚገባቸው እስኪረክሱ ድረስ ማርከሻውን መጋት ተገቢ ነው እላለሁ።

"ሳስበው ሳስበው ኢህአዴግ ታሟል" የሚለን የእፉኝቱ ልጅ አቤ ቶኪቻው ነው፡፡ እኔ ደግሞ ሳስበው ሳስበው አቤ ከህመምም አልፎ አብዷል፡፡ እብደቱንም ከእርሱ የኢህአዴግ የህመም ምልክቶች አንፃር እየፈተሽኩ አረጋግጣለሁ፡፡ ለጥቄም የተስፋዬን "የቦሌዋ ብስኩት" መርዛማነትና ከመርዛማ ከረሜላዎች ወደ መርዘኛ ብስኩቶች የተደረገውን ሽግግር ከነመነሻ ምክንያቱ አሳያለሁ፡፡

የአንድ ሥርዓትና አስተዳደር መታመም ወይም አደጋ ላይ የመውደቅ ምልክቱ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ /ምንም እንኳን ጉዳዩ ሰፊና ዝርዝር ቢሆንም/ መሠረታዊ ከሆኑት እና ከአቤ ምልክቶች አንፃር መዝነን መጀመሪያ ማየቱና መመለሱ ጠቃሚ ነው፡፡

በአቤ ቶክቻው ህመሙ የተረጋገጠውና ምልክቱም ታይቶበታል የተባለው ኢህአዴግ እንደ ሥርዓት በየዓመቱና ወቅቱ መሻሻሎች እያሳየ፣ ከድክመቱ እየተማረና እየገዘፈ የሚሄድ፤ ጥንካሬዎቹንም የበለጠ እያጐለበተና ራሱን እያደሰ የሚሄድ ድርጅት ስለመሆኑ በተግባር የታየና ዓለም የመሰከረለት እውነታ ነው፡፡

ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ የነደፋቸውን ፕሮግራሞች ያስፈጽሙልኛል የሚላቸውን አመራሮች ሲሰይም ተሿሚውን በበርካታ ድርጅታዊ ተልዕኮዎችና የማስፈጽም ብቃት ፈትሾና መዝኖ ነው፡፡ በተመሣሣይም ከሥር የሚገኙ አባሎቹንና መካከለኛ አመራሩን ሳይቀር እያበቃና እየተካ የሚሄድበትን አቅጣጫም ዘርግቶ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው፡፡ በዚህ ድርጅታዊ የአሠራር ሥርዓቱም

ውጤታማ መሆን የቻለና ለሌሎችም ልምዱን እስከማካፈል ደረጃ የደረሰ ብቃት ያለው ድርጅት ነው፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ኢህአዴግና በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በመዘንጋትና የተሰጣቸውን ድርጅታዊ አደራ መብላት ሲጀምሩ ኢህአዴግ በኖረበትና እዚህ ደረጃ ላይ ባደረሰው የግምገማ ሥርዓቱ ተጠቅሞ እንደየጥፋቱ አመራሩን ከምክር ጀምሮ እስከ ኃላፊነት ማንሳት የሚደርስ እርምጃ ይወስዳል፡፡ ይህ ደግሞ ለኢህአዴግ አዲስ ያልሆነና ሁሉም አመራር በዚህ ቅኝት እየተቃኘ ከዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ያውቀዋል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን አብዛኞቹ የኢህአዴግ አመራሮች ተገምግመው ኃላፊነታቸውን ሲነጠቁ ከጥፋታቸው ተምረውና ራሣቸውን አርመው ደግሞ ወደ አመራርነት እንደገና የሚመጡበት አሊያም ደግሞ ጥፋታቸውን ተቀብለው ከአቅማቸው በላይ የሆነን ኃላፊነት ላለመውሰድ አረጋግጠው አብረው ከድርጅቱ ጋር የሚጓዙ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የሰው ተፈጥሮ ነውና የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣት የተሳነው እንደሆነ በተጨባጭ አምኖና ተቀብሎ ወንበሬ ተወሰደ ብሎ የሚያኮርፍም አይጠፋም፤ ነገር ግን በኢህአዴግ ውስጥ እንዲህ ዓይነቶቹ ጥቂት ናቸው፡፡

ስለሆነም አኩራፊና ኮብላይ ለኢህአዴግ ምኑም አይደለም፡፡ ራሱን ለማረም ለተዘጋጀና ለሚሰራ ኃይል የኢህአዴግ በር ሁሌም ክፍት ነው፡፡ ለማይሰሩትና ተልመጥምጠው በሕዝብ ላይ ለመኖር ለሚሹቱ ደግሞ የኢህአዴግ በር የተከረቸመ ነው፡፡ ስለሆነም አንዳንዶች ከስህተታቸው በመታረም የተከረቸመውን በር ማስከፈት ሲቻላቸው መኮብለልንና መሸሽን መምረጣቸው በእርግጥም የሚያመለክተው የኢህአዴግን እርምጃ ትክክለኛነትና የግለሰቦቹን ራስ ወዳድ  አስተሳሰብ  ቢሆን እንጂ የኢህአዴግን ህመም አይመስለኝም፡፡

ይህን ያወሳሁት አቤ ቶክቻው ስለኢህአዴግ የህመም ምልክት ያቀረባቸውን ሁለት የኢህአዴግና የቀድሞ ከፍተኛ አመራሮች በተመለከተ መንደርደሪያ እንዲሆነን ነው፡፡

በአቤ በኩል ስለኢህአዴግ የመታመም ምልክቶች ሆነው የቀረቡት የቀድሞው የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባና የማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ አቶ ከፍያለው አዘዘና የቀድሞው የገቢዎች ሚኒስትር ጌታቸው በላይ ናቸው፡፡

በእኔ በኩል እነዚህ ግለሰቦች መኮብለላቸውን ቀርቶ ከአገር ስለመውጣታቸውም በመንግሥት በኩል የተሰጠ መግለጫና የቀረበ ማስረጃ ያለ አይመስለኝም፡፡ ሆኖም ግን የተለያዩ የውጭና የአገር ውስጥ ፕሬሶች ሁለቱም ግለሰቦች በአገረ አሜሪካ እንደሚገኙና በተለይም አቶ ጌታቸው በላይ ሥራ

መጀመራቸውን ጭምር ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህኑ ፐሬሶች አምነን እንኳን ብንሞግት የእነዚህ ግለሰቦች መሄድና መምጣት ለኢህአዴግ እንኳን ህመም ሊሆን ቀርቶ የጉንፋንም ያህል ህመም ሊሆን የሚችልበት አግባብ አይታየኝም፡፡

አቶ ጌታቸው ሄደዋል እስከተባሉበት ጊዜ ድረስ የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተርና የህወሓትም ከፍተኛ አመራር መሆናቸውን አውቃለሁ፡፡ አቶ ከፍያለውም ቢሆኑ በአዲስ አበባ አስተዳደር በኩል የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ተስኗቸው በመገኘቱ ድርጅቱ ገምግሞ እንዳወረዳቸው በግልጽ ከተሰጠው የመንግሥት መግለጫ ታውቋል። ሆኖም ግን ብሔራዊ ድርጅታቸው በሆነው ብአዴን ውስጥ ካላቸው ኃላፊነት ስለመነሳታቸው እና ስላለመነሳታቸው የተሰጠ ይፋዊ መግለጫ የለም፡፡

ዳሩ ግን ሄደዋል በሚለው ላይ ተስማምተን ስለሆነ እየሞገትን ያለነው የእነዚህ ሁለት ግለሰቦች አምስት ሚሊዮን አባላት ካሉትና በርካታ ድንቅና ጥበበኛ በሆኑ አመራሮች ለተሞላው ኢህአዴግ የህመም ምልክቶች ሆነው መቅረባቸው አይደለም፡፡ ለእኔ ያሳዘነኝ አሁን ኢትዮጵያ ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታና ከድህነት ጋር ከተያያዘችው እልህ አስጨራሽ ትግል አንፃር ያጠፉ ሰዎች ላይ ተገቢ እርምጃ ሲወሰድ በእነ አቤ በኩል ለኢህአዴግ ውዳሴ አለመቅረቡ ነው፡፡ ህመምተኛ እንኳን ቢሆኑ ውዳሴ ለኢህአዴግ ማቅረብ ባልተሳናቸውም በነበር፤ ግን ሳስበው ሳስበው አቤና ግብረ አበሮቹ አብደዋል፡፡

ሌላ ደግሞ ተጨማሪና ትክክለኛ የእነ አቤ እብደት መገለጫ የሆነ አጀንዳም ከዚሁ ከአቤ መጣጥፍ ላይ እናንሳ፡፡ ስለኢህአዴግ መታመም አቤ በምልክትነት ያነሳው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩን አቶ ጁነዲን ሣዶን ነው፡፡

አቶ ጁነዲንን በተመለከተ ጉዳዩን የያዘው የሚመለከተው አካል ይፋዊ መግለጫ ባይሰጥም ቢያንስ ራሣቸው የተሰጣቸውን መንግሥታዊ ኃላፊነት ተገን በማድረግ ከሣውዲ ኤምባሲ ላይ ኪራይ እንደሰበሰቡና በቀዬያቸው ላይ መስኪድ መስራታቸውን አምነዋል፡፡ ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ላይ፤ እነ አቤም ቀደም ብለው በፍትህ ጋዜጣ እንደሚለፍፉት ኪራይ ሰብሳቢነት የሥርዓቱ አደጋ በሆነበት ሁኔታ ላይ አቶ ጁነዲን ላይ አብዮታዊ እርምጃ መወሰዱ ኢህአዴግን የሚያስወድስ፤ እንዲሁም ኢህአዴግ ችግሮቹን እየለየ ውስጥ ለውስጥ የተሰገሰጉ መጣጮችን እየቆራረጠ በመፈርጠምና በማይናወጽ ጽኑ መሠረት ላይ እየተገነባ መሆኑን ቢያመላክተን እንጂ አቤ እንደሚለው በአመንምን መጠቃቱን አይመስለኝም፡፡ አቤማ "የቤት ጣጣም አለበት" ሲል ለኢህአዴግ ይመርቅለታል፡፡ ዳሩ ግን በቤት ጣጣ የታጠሩትና ጣጣቸው እያሳበዳቸው የሚገኙት የትኞቹና እነማን እንደሆኑ እናውቃለን፡፡ የቤት ጣጣ ባለልምዶች አበባ ቶላና ተስፋዬ ገብረአብን የመሰሉ እብዶች እንጂ በኢህአዴግ ቤት ውስጥ የለም፡፡ ቢኖርማ ኖሮ በነፃ ባደላችኋቸው መርዛማ ከረሜላዎች ተለክፎ

በነበረና እንደምኞታቸው ፈራርሶ ባየነው፡፡ ግን የሆነውና የምናየው ሁሉ የግልባጩን ነው፡፡ እነ አቤ ደግሞ ከአገር ሲወጡ  እብደታቸው እየባሰ መሄዱን ነው፡፡

እናማ እልሃለሁ አቤ የኢህአዴግን ከሥልጣን በፊት የነበረው የትግሉን ጊዜ እንተወውና፣ በሥልጣን ላይ የቆየባቸውን 21 ዓመታትም እንዝለለውና ቢያንስ አንተ ለአቅመ ጽሁፍ ከደረስክ በኋላ ያለውን ኢህአዴግ እንኳ ማስተዋሉን ካልነጠቀህ መለስ ብለህ ብትመለከተው እየመነመነ ሳይሆን እየፈረጠመ፣ እያቈበ ሳይሆን አውራ መሆን በሚያስችለው መንገድ ላይ እየሄደ መሆኑን ትደርስበታለህ፡፡ በአንፃሩም የአንተንና የግብረ አበሮችህን ጊዜም ከአቅመ ጽሁፍ ዘመናችሁ ጀምሮ ተመልከተው፣ ጉዟችሁ ሁሉ የኋሊት፣ ቁመናችሁ ሁሉ ቁልቁል፣ ራስ ምታታችሁ ሁሉ እብደት፣ መርዶ ነጋሪነታችሁ ደግሞ ወደ ጥሩንባ ነፊነት የተሸጋገረ መሆኑን ትደርስበታለህ፡፡ ስለሆነም ነው ሳስበው ሳስበው አቤና ተስፋዬ ገብረአብ አብደዋል የምለው፡፡
የአበበ ቶላ እብደት አሁንም እንደቀጠለ ነው "ኢህአዴግ ዲ" የሚባል ፓርቲ ለማቋቋም የፈለገ አንድ የኢህአዴግ አባል የሆነ ጓደኛዬ ምክንያቱን ሲያስረዳኝ "በህወሓት ተወረናል ስለሆነም ዲ አልባውን ኢህአዴግ "በኢህአዴግ ዲ" መለወጥ አለብን" ብሎ አጫወተኝ ሲል ይተርካል። ዳሩ ግን ለአቤ ማንም አላጫወተውም፡፡ ።በመጀመሪያ ይህን ያጫወተው የኢህአዴግ አባል የሆነ ግለሰብ ከሆነ "ዴ" ሞክራሲን "ዲ" ሞክራሲ አይለውም። ስለሆነም ጥራዝ ነጠቋ አቤ የኢህአዴግን መመናመን ለማመላከት የግብረ አበሯን ተስፋዬ "የሰው ነገረኝ ስታይል" በመከተል ዴሞክራሲ አልባው ኢህአዴግ ለማለት በሰው ነገረኝ አስታኮ "ኢህአዴግ ዲ"  የምትባል አዲስ መርዝ አስመጣ። ዳሩ ግን ሁሉም አውቃችኋልና እዚያው በፀበላችሁ እያለ ነው።

ወደሁለተኛው እብድ እናምራ፡፡ ተስፋዬ ገብረአብ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ለማውሳት እንደሞከርኩት ተስፋዬ ቀደም ብሎም ቢሆን ሥነ ጽሁፋዊ ክህሎቱን ተጠቅሞ በሚጽፋቸው ድርሰቶቹ ሳይቀር ፌዴራላዊ ሥርዓቱን ለማናጋትና በብሔሮች መካከል ግጭት ለመቀስቀስ ሰርቷል፡፡ ከጀርባው ላይ ሆኖ የሚጋልበውን ሻዕቢያም አድርሰኝ በተባለው ቦታ ላይ ለማድረስ በየድረ ገጹ "ማስታወሻ" ሲል ብዙ ለፍቷል፡፡ አልሳካ ያለውና የአለቆቹ ቅጣት ያሰጋው ተስፋዬ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ህልፈተ ህይወት ተከትሎ ብሄር ተኮር መርዞች የተቀቡ ከረሜላዎችን በነፃ ለማደል ያደረገው ጥረት በኢህአዴግ ውስጥ በተደረገ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር፣ በሕዝቡ ቁርጠኛ አቋምና ድጋፍ ሲከሽፍ ሹመት አሰጣጡን ተንተርሶ ደግሞ በየጥጋጥጉ ሲርመሰመስና ሲፎትተን ከርሟል፡፡

አሁን ከድረ ገጽ በመሻገር ለሆዳቸው ባደሩ መጽሄቶች የቻለውን አምድ ሁሉ መከራየትና ትንፋሹን አሟጦ መጠቀም አማራጭ የሌለው መሆኑን አምኖበታል፡፡ ስለሆነም በአጭር ልቦለድ ቆብና በትዝታ ካባ ያለፉ ታሪኮችን /ውሸት መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ/ መገረብ ጀምሯል፡፡ ግን አገራረቡ አያምርም። ተራና የወረደ ነው፡፡ ለነገሩ  ከአበደ ሰው የሚጠበቅ ነው፡፡

"የቦሌዋ ብስኩት" ይላል የተስፋዬ መጣጥፍ፡፡ አስነባቢውና አምዱን አከራዩ ደግሞ "ቆንጆ" የተባለው አገር በቀል መጽሄት ነው፡፡ የዚህ መጣጥፍ ግብ የሚታወቅ በመሆኑ አልገረመኝም። የደነቀኝ ነገር ተስፋዬ መጣጥፉን ለመፃፉ መነሻ የሕሊና  መንፃትን ከመሻት የመነጨ መሆኑን መግለጹ ነው፡፡ በእርግጥ ተስፋዬ ይህቺን የሕሊና መንፃት እንደ ሽፋን መጠቀሙ ቆንጆ መጽሄት አዘጋጆችን ለመሸወድ  ሊጠቅመው ይችላል። ምክንያቱም የትኞቹም የአገሬ ጋዜጦች ተስፋዬን ሲያወግዙ እንጂ ሲያሞግሱት አንብቤ ወይ ሰምቼ አላውቅምና። ነውጠኛ የነበረችው ፍትህ ጋዜጣም እንኳ ከሻዕቢያ እንጂ ከተስፋዬ ጋር አብራ (“ብ” ጠብቆ ይነበባል) ተመልክቻት አላውቅም፡፡

የሆነው ሆኖ ተስፋዬ በዚህ መጣጥፉ እጅግ ወደ ኋላ ተስቦ አንድ የጥምቀት በዓል “ትዝታውን” ይተርካል፡፡ ብስኩት የተባለችና "ሊፍት" የሰጣት ግለሰብ የተስፋዬ መርዝ አቀባይ ገፀ ባህሪ ሆና ተስላለች፡፡ እናም ይህቺን ልጅ ተስፋዬ የመጨረሻ ድሀ ነች ሲል ገጽታዋን እና አልባሟቷን ማሳያ በማድረግ ይገልጻታል፡፡ ቀጥሎም  ያታዊ ግንኙነት አምሮትም እንደነበር በማውሳት መርዙን የተለያዩ ቦታዎች ላይ ይቀባባል፡፡ እናም ተስፋዬ እንደሚለው ሰፈሯ ካደረሳት  በኋላ እናቷ የታመመችባት መሆኑን ገልጻለት ይረዳት ዘንድ ለመነችው፡፡ ከዚያም ተስፋዬ እቤቷ ድረስ ዘልቆ ይገባና የልጅቱን እናት ይጐበኛል፡፡ የልጅቷ አባት የደርግ ሠራዊት መሆኑንና በወያኔ የተበላ መሆኑንም በሳላቸው ታማሚና አስታማሚ ገጸ ባህሪያቶቹ በኩል ይተርካል፡፡ ከዚያም በሌላ ቀን ገጸ ባህሪያቶቹን ተመልሶ እንደሚጐበኛቸው ቃል በመግባት ተሰናብቶ ይወጣና ባለመመቻቸት ቃሉን መጠበቅ እንደተሳነው  ነግሮን አንድ ቀን ምሽት ብስኩት “ሴተኛ አዳሪ” ሆና ሲጋራ እያጨሰች መንገድ ላይ እንዳያት ይገልጻል፡፡

አይ ተስፋዬ፤ ተስፋዬ የፈለገው በብስኩትና በእናቷ በኩል አቋርጦ ይህቺው ኢትዮጵያ ትከሻ ላይ መንጠልጠልን ነው። እንዴ ተስፋዬማ የሚፀፀት ሕሊና ኖሮትም አያውቅም። ቢያውቅና የፀፀትን ትርጉም ቢረዳማ በአንድ ወቅት የተስፋዬን የጋዜጠኛ ማስታወሻ ተንተርሰው አንድ ስማቸውን የማላስታውሳቸው ታጋይ "ያልከው ሁሉ እውነት ይሁን እንበልና ምነውሳ ያን የበተንከውን ቤተሰብ፣ ያን ያስገደልከውን ዜጋ ዘነጋኸው?" ሲሉ ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ ቢሰጥና ተጸጽቶ ይቅርታ ባለ መልካም በነበር።

ግን የተስፋዬ ጉዳይ ይህ አይደለም፡፡ የተስፋዬን ሥነ ጽሁፍ ህይወት ከኢትዮጵያ ጋር አቆራኝተን ታሪካዊ ዳራውን ስንፈትሽ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያን ማንኳሰስ፤ ያሳደገችውን ኢትዮጵያን ከምድረ ገጽ ማጥፋት፤ ሕዝቦቿን ማጫረስ፤ ብሔር ብሔረሰቦቿን ማባላት ከዚያም ሻዕቢያ የሰጠውን ተልዕኮ ማሳካትና ከኢሣያስ አፈወርቂ ጥርስ ማምለጥ ነው፡፡

ተስፋዬ የሚያውቃቸውን እና ራሱም ተሳታፊ የነበረባቸውን ፖለቲካዊ ሁነቶች በተመለከተ ምንም እንኳን የራሱን ሚናዎች ቢደብቅምና ቢሸፍንም አጣጥሞ ይጽፋል፡፡ የሌለባቸውን ሁነቶች ደግሞ ከወቅታዊው የኢትየጵያ ሁኔታ ጋር በቀጭን ገመድም ቢሆን አገናኝቶ አሊያም "እገሌ ነገረኝ"

"ከእገሌ ሰማሁ" ብሎ ጉዳዩ ነፋስ አመጣሽ ወሬ እንደሆነ አስመስሎ መርዙን ለመርጨት ፋታ እንኳን አይወስድም።

ሆኖም ግን በሂደት የተስፋዬን የተደበቀ አጀንዳና ሴራ የተገነዘቡ በርካታ ፀሀፊያን ተስፋዬን አንቅረን ልንተፋው ተገቢ መሆኑን በማስረጃ አስደግፈው ያስነበቡን ገና ከቢሾፍቱ ቆሪጦች ማግሥት ነው፡፡ የጋዜጠኛው ማስታወሻው ላይ ስንመጣ ደግሞ በግልጽ የተመለከቱትን መርዘኛ ከረሜላዎች ነቅሰን ለማውጣት የግድ ሥነ ጽሁፋዊ ክህሎት አልተጠበቀብንም ነበር፡፡

አሁን ደግሞ የዲያስፖራውን የልብ ትርታ እያደመጠና የአገራችንን የተቃውሞ መንደር እያሸተተ የተልከሰከሱ ጽሁፎችን እያልከሰከሰልን ነው፡፡

ተስፋዬ ሀሳቡ በሀሳብ ሲመታና ሴራው በሴረኛ ሥነ ጽሁፋዊ ሥልት ሲብጠለጠል የሚያመራው ገጸ ባህሪያት ስሎ ራሱን በማውጣት በአቋራጭ መንገድ ኢትዮጵያን ማጠልሸት ነው፡፡

"የጥምቀቷን ብስኩት" ተስፋዬ በእርግጥም አግኝቷት ነበር ብለን እንኳን ብንወስድ የ1988ቱን ጥምቀት ከ2005ቱ ጥምቀት ጋር በማመዛዘን የኢትዮጵያን ገጽታ ማመላከት አይቻልም፡፡ የፎረሸና መንደራዊ የመመዘኛ አግባብ ነው የሚሆነው፡፡ ይህም ቢቀር ደግሞ የነብስኩት ቤተሰብን ለናሙና ወስዶ የኢትዮጵያን ድህነት ለመስበክ መሞከር አላዋቂ ሳሚነት ነው፡፡

ብስኩትን የመሰሉ ሰዎችንም በብስኩት አባት አስታኮ ወያኔ ላይ ጥላቻ እንዲያስወሩ መግፋት “ለማያውቅሽ ታጠኝ” ነው፡፡ ጅልነትና እብደትም ነው፡፡

አቤ አብዶ ተገምግመው የወረዱ አመራሮችን ለኢህአዴግ የህመም ምልክት እንዳደረጋቸው ሁሉ ተስፋዬም የብስኩትን እናት ህመምና የብስኩትን ድህነት የኢትዮጵያ መገለጫ አድርጎ መውሰዱ በተመሣሣይ የእብደት ደረጃ ላይ የሚገኙ ስለመሆናቸው ያረጋግጥልናል፡፡